# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 206 ሚያዝያ 18 2004 ገጽ 1


**መለስ ዜናዊ ከሥልጣን እስካልተወገደ ድረስ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች አንዳችም መብት፤ አንዳችም ነፃነት እንደማይኖራቸው ማመን ይገባል። ይህ እምነት ደግሞ እያደር በሁሉም ወገኖች ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ ነው።**

**ግንቦት 7፣ ሙስሊምም ሆነ ክርስቲያን የሆንን ኢትዮጵያዊያን በሙሉ "መለስ ዜናዊ ቁርጥህን እወቅ፤ እኛ አንለያይም!!!" እንድንለው ይጠይቃል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በፈጠረው ኢኮኖሚያዊ ችግር ከፉኛ በተመታው አድስ አበባ ከተማ ውስጥ "ተነሱ የሚል ጥሪ ወረቀት" በስፋት እየተበተነ መሆኑ ተገለጸ

የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በሚከተለው አድሎአዊ አሰራር ለከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉስቁልና በመዳረጋቸው ተስፋ ቆርጠው እራሳቸውን በተለያየ ሁኔታ እያጠፉ ያሉ ዜጎች ቁጥር እየተበራከተ መምጣቱ እየተዘገበ ባለበት በአሁኑ ሰዓት፤ የአድስ አበባ ፖሊስ ባልደረባ የነበረ አንድ ወጣት ከትናንትና በስቲያ ማክሰኞ ሚያዚያ 16 ቀን 2004 እራሱን በእሳት ማጋየቱን ተከትሎ ሁኔታው እንዲጣራ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ የሞከሩ የ6ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በፖሊስ መበተናቸው ታወቀ።

አዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው የዳግማዊ ምኒልክ ሃውልት ፊት ለፊት ባለው የከተማ አውቶቡስ ማቆሚያ አጠገብ እራሱ ላይ እርምጃ የወሰደው ዳዊት የተባለው ይህ ወጣት እርምጃውን ከመውሰዱ በፊት አላፊ አግዳሚ በበዛበት የአውቶቡስ ማቆሚያ ፈርማታ አካባቢ አገሪቱ ውስጥ በሰፈነው አድሎአዊነትና አፈና ምክንያት ለመኖር ተስፋ የቆረጠ መሆኑን ድምጹን ከፍ አድርጎ ሲናገር እንደነበረና ወዲያውኑ በእጁ ይዞት የነበረውን ፕላስቲክ ጀሪካን ከፍቶ በውስጡ የነበርውን ነዳጅ ራሱ ላይ በማርከፍከፍ ክብሪት እንደለኮሰ የአይን እማኞች ተናግረዋል።

በግምት በመጨረሻዎቹ 20 የእድሜ ክልል ውስጥ ይገኛል የተባለው ይህ ዜጋ በራሱ ላይ የሎከሰውን እሳት በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ለማጥፋት ይረባረቡ በነበረበት ሰዓት "ህዝብና መንግሥት በምሬት ማለፌን እንዲያውቅልኝ መሞት እሻለሁና አታድኑኝ" በማለት (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በቻይና እርዳታ ኢትዮ ቴሌኮም ወደ ወያኔ የስለላ ተቋምነት መቀየሩ የሚያረጋግጥ ጽሁፍ ወጣ

"አዲሱ ቴሌ" እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ)" በሚል ርዕስ የህዝብ ሃብት የሆነው ቴሌ እንዴት ወደ ወያኔ የስለላ ተቋምነት እንደተቀየረ የሚያስረዳ ሰነድ በአዲስቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ተዘጋጅቶ ይፋ ሆነ። በዚህ መረጃ መሠረት ቴሌ ትልቁ የወያኔ የደህንነት ተቋም ሆኗል።

የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የአገልግሎት አሰጣጡን ለማስፋትና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ሲነሳ በመጀሪያ ፊቱን የሰጠው ለምዕራብ አገር የቴሎኮም ኩባንያዎች ነበር። ሞባይል፣ መደበኛ ስልክ፣ ብሮድባንድና ገመድ አልባ የስልክ መስመሮችን ለመዘርጋት በተዋረድ ለተያዘው እቅድ እንደ ቅደም ተከተላቸው ጨረታ ሲወጣ አሸናፊ የነበሩት ኤሪክሰን፣ ኖኪያ፣ ሲመንስ፣ አልካቴልና የመሳሰሉ የምዕራብ አውሮፓ የቴሌኮም ሲሆኑ አንድም የቻይና የቴሌኮም ኩባንያ አልነበረም በማለት ሰነዱ ያብራራል

ሆኖም ግን መለስ ወደ ቻይና ደርሶ ሲመለስ ብዙ ነገሮች መቀየራቸው ሰነዱ ያመለክታል። የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽንን ዘመናዊ ለማድረግ በሚል ሰበብ ዜድቲኢ የተሰኘ የቻይና የቴሌኮም ኩባንያ 1.5 ቢሊዮን ዶላር ከቻይና ኤዚም ባንክ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ይዞ እንደሚገባ መናፈስ ጀመረ። ጉዳዩ ከቴሌ ጋር እየሠሩ የነበሩት ምዕራባዊያን ኩባንያዎችን አስደነገጠ። በወቅት ለተፈጠረው ስጋት የተሰጠው መልስ "የዓለም ቴሌኮም ቴክኖሎጂ አንዱ ከሌላው ጋር እንዲግባባ ተደርጎ የሚሠራ ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ በመሆኑ ስጋት ሊፈጠር አይገባም" የሚል ነበር። በሌላ ወገን ግን የቻይና የቴሌኮም ኩባንያዎች እንዲገቡ የተደረገው ቀደም ሲል ሲሰሩ የነበሩትን የቴለኮም ኩባንያዎች በማግለል የምዕራብ አገሮችን የስለላ መዋቅር መሸሽ በወያኔ በድርጅት ደረጃ ስለታመነት መሆኑ ሰነዱ ያትታል።

በመቀጠልም፤ በብርጋዴር ጄኔራል ተክለብርሃን ወልደአረጋይ የሚመራው በቀጥታ ተጠሪነቱ ለመለስ ዜናዊ የሆነው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ) ዜድቲኢ ከዘረጋው የቴሌኮም አገልግሎት ጋር በቀጥታ የተዛመደ ቴክኖሎጂ ከቻይና አስመጥቶ ሞባይል፣ መደበኛ ስልክ፣ ኢሜል፣ ፌስ ቡክና የመሳሰሉትን መገናኛዎች በመሰለል ሥራ ላይ መጠመዱን ሰነዱ ያጋልጣል።

በዚህም ምክንያት የአገር አንጡራ ሃብት የሆነው ቴሌ ዛሬ ወደ ወያኔ የስላላ ተቋምነት መቀየሩን ሰነዱ ያብራራል።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ያቀረበውን የመብት ጥያቄ በሃይል ለመጨፍለቅ በዝግጅት ላይ መሆኑ ታወቀ

በሃይማኖታቸው ጉዳይ መንግስት ጣልቃ እንዳይገባና ከምዕመኑ ፍላጎት ውጭ በሃይል የተጫኑባቸውን የመጂሊስ አመራሮች ህዝብ በሚመርጣቸው አካሎች እንዲተኩ በሰላማዊ መንገድ ላለፉት 3 ወራት ሙስሊም ወገኖቻችን እየጠየቁ ያለውን የመብት ጥያቄ በሃይል ለመደፍጠጥ የመለስ ዜናዊ አስተዳደር በዝግጅት ላይ መሆኑን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ።

እንደ ታማኝ ምንጮቻችን መረጃ ከወያኔ ቱባ ባለሥልጣናት አንዱ የሆነው ስዩም መስፍን ለሃያ አመታት የመራውን የውጪ ጉዳይ ሚንስትርነት ሥልጣኑን ለቆ የወያኔ ባለሥልጣናትና የንግድ ድርጅቶቻቸው የአገሪቱን ገንዘብ ወደሚያሸሹበት አዲስቷ ሽሪክ አገር ቻይና ሲመደብ ለይስሙላ ለተተካው ሃይለማሪያም ደሳለኝ በታኮነት የተቀመጠው ብርሃኔ ገብረኪርስቶስ ፤ በአዲስ አበባ የሚገኙትን የምዕራብ ዲፕሎማቶች አንድ በአንድ እየተገናኘ አገሪቱንና የቀጠናውን ሰላምና መረጋጋት ሊያደፈርስ የሚችል የእስልምና አክራሪነት መረብ በአገሪቱ መዘርጋቱን እየሰበከ እንደሚገኝ ታውቆአል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከሰፈነው የፖለቲካ አፈና በተጨማሪ የኑሮ ውድነቱ እያስከተለ ባለው ማህበራዊ ቀውስ አንድ ቀን ሊፈነዳ የሚችል ህዝባዊ አመጽ እንደሚኖር በመገመት ሁኔታውን በቅርበት እየተከታተሉ ያሉ ምዕራባዊያን ዲፕሎማቶች በተለይ ሁለቱ የሲዊዲን ጋዜጠኞች በሽብርተኝነት ተከሰው የ11 አመት እስራት ከተፈረደባቸው ወዲህ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሽብርተኝነትና አክራሪነት ትርጉም ፍጹም የማይዋጥላቸው ደረጃ ላይ መድረሱን የሚናገሩ ምንጮች ኢትዮጵያ ውስጥ የሃሳብ ነጻነት ለማፈን ተብሎ በእነ ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ፤ እስክንድር ነጋ፤ ውብሼት ታዬና በሰላማዊ ታጋዮች በእነ አንዱአለም አራጌ ላይ የተፈበረከው ተመሳሳይ ክስ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ የነበራቸውን እምነት እንደሸረሸረው በዚህም የተነሳ የብርሃኔ ገብረ ክርስቶስን ውትወታ ምንም ቦታ እንዳልሰጡት ገልጸዋል።

መለስ ዜናዊ ባለፈው ሳምንት ለፓርላማ ተብዬው ስብስብ በሰጠው መግለጫ የሙስሊሙን የመብት ጥያቄ የጥቂት አክራሪዎች ጥያቄ ነው ከማለት አልፎ "የአልቃይዳ ህዋስ በአገሪቱ ውስጥ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ በልማት ሥም የዋልድባን ገዳም ለማፍረስ የሚያደርገው ተግባር እንዲገታ በቶሮንቶ ካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በሠላማዊ ሰልፍ ጠየቁ

ወያኔ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቅርጽ ለመናድና የእምነት ተቋማትን ለማፍረስ የጀመረውን ዘመቻ ለማስቆም ኢትዮጵያዊያን የተቃውሞ ድምጻቸውን እንዲያሰሙ በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የቶሮንቶ ከተማና አካባቢዋ ነዋሪዎች መገኘታቸውን ከስፍራው የደረሰን ዜና አመለከተ።

ለስኳር ፋብሪካ ምርት ተብሎ የዋልድባን ገዳም ለማፍረስ ወያኔ እየወሰደ ያለው እርምጃ ያስቆጣቸው ሰላማዊ ሰልፈኞች **በአሰቦት** እና **በዝቋላ** ገዳማት ላይ ተመሳሳይ ጥፋት እየተፈጸመ መሆኑን አውግዘው ድርጊቱ ታሪክን፤ ሃይማኖትን እና ለዘመናት ተጠብቀው ያሉ እንስሳትና እፀዋት ላይ ከፍተኛ ውድመት የሚያስከትል ስለሆነ በአስቸኳይ እንዲቆም ጠይቀዋል።

እየደረሰ ያለውን ውድመት ለመቃወም በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክረስቲያን በጠራው ሠላማዊ ሰልፍ የተለያዩ የሰባዊ መብት ድርጅት ተወካዮች የተገኙ ሲሆን በሠላማዊ ሰልፉ ላይ ተለያዩ መንፈሳዊ መዝሙሮችና መፈክሮች ተደምጠዋል።ሃይል የእግዚአብሔር ነው፣ ተው፤ ተው በሏቸው!የዋልድባ ገዳም የሰኳር ፋብሪካ አይሆንም፤ የአብያተ ክርስቲያናትና የገዳማት ቃጠሎ ይቁም፣ ካናዳ አምባገነኖችን መርዳት አቁሚ፣ መለሠ ዜናዊ ብሔራዊ ጠላት ነው ወዘተ የሚሉ መፈክሮች አስተጋብተዋል።

ሰላማዊ ሰልፈኞቹ በአገራችን ውስጥ በአብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋት የሚዘረዝር ደብዳቤ አዘጋጅተው በኦታዋ ለካናዳ ጠቅላይ ሚንስትር፤ ለውጭ ጉዳይ ሚንስተር እና ለኢሚግሬሽን ሚኒሰተር በእጅ ከመስጠታቸው በተጨማሪ ለተለያዩ አለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግሥታት መላካቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

በቶሮንቶ ከኦንታሪዮ ክፍለአገር ፓርላማ ፊት ለፊት የተነሳው ይህ ሰላማዊ ሰልፍ መንፈሳዊ መዝሙርና መፈከር እያሰማ ወደ ቶሮንተ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በማምራት የተለያዩ መፈክሮችን ካሰማ ቦኋላ ጉዞውን ወደ አሚሪካን ቆንሲላ ጽ/ቤት በማቅናት የአሚሪካ መንግሥት ለአምባገነኑ የወያኔ መንግሥት የሚሰጠውን እርዳታ እንዲያቆም በመፈከር በመጠየቅ የተቃውሞ ደብዳቤውን አስገብቶ ሰልፉን በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁ ታውቆአል።

## አንለያይም !!!

ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያዊያን ለመከፋፈል ምን ያህል ተግቶ እየሠራ እንደሆነ ሰሞኑን "ፓርላማ" ብሎ ለሚጠራው ግዑዝ ስብስብ የተናገረውን ማጤን ይበቃል።

መለስ በዚህ ንግግሩ መብቶቻቸውን የጠየቁ ሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን በሽብርተኝነት ፈርጇል። "አክራሪ ሙስሊሞች መጡብህ፤ ተነስ" ዓይነት የማስፈራሪያ መልዕክት ለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ለማስተላለፍ ሞክሯል። ለዚህም እንዲጠቅመው "የአልቃይዳ ህዋስ አግኝተናል"፤ "የአክራሪዎቹ ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ እስላማዊ መንግሥት ማቋቋም መሆኑ ደርሰንበታል" ሲል ቀበጣጥሯል።

መለስ ክርስቲያኖችን በሙስሊሞች እንዳስፈራራ ሁሉ ሙስሊሞችንም በክርስቲያኖች ለማስፈራራት ጥሯል፤ ክርስቲያኖችንም በሽብርተኝነት ፈርጇል። "አክራሪ ኦርቶዶክሶች 'አንድ አገር አንድ ህዝብ' ብለው ተነስተዋል፤ ዓላማቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ የክርስቲያን መንግሥት ማቋቋም እንደሆነ ደርሰንበታል" ሲል ዘላብዷል። ለነገር ማጣፈጫነትም ማኅበረ ቅዱሳንን በማስረጃነት ጠቅሷል።

የመለስ ንግግር ዓላማ ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን፤ ክርስቲያኖች ደግሞ ሙስሊሞችን እየፈሩ እና እርስ በርስ በዓይነ ቁራኛ እየተጠባበቁ እርሱ ተደላድሎ እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። የመለስ ዜናዊ ዓላማ የሁለት ትላልቅ ሃይማኖቶች ተከታዮች ሲጣሉ እሱ በመሃል "አስታራቂ ዳኛ" ሆኖ መገኘት ነው።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ ከእንግዲህ ለመለስ ዜናዊ መሠሪ ተንኮል የሚፈታ አይደለም። ክርስቲያኑ የሙስሊሞች ጥያቄዎች የመብት ጥያቄዎች መሆናቸውን ተገንዝቧል። ሙስሊሙም የክርስቲያኑ ጥያቄዎች የመብት ጥያቄዎች መሆናቸው ያውቃል።

ሁለቱም ሃይማኖቶች እና ምዕመናኑ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ በደል ደርሶባቸዋል፤ እየደረሰባቸውም ነው። በመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሙስሊሞች የእምነት ነፃነት ተደፍሯል። ሙስሊሙ ማኅበረሰብ መሪዎቹን የመምረጥ መብቱ ተነፍጓል፤ የእምነት ተቋማቱ ነፃነት ተገፏል። ይህንን ሃቅ ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖችም ያውቃሉ። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችን የእምነት ነፃነት ተጋፍቷል፤ የሃይማኖት አባቶችንና ምዕመናንን ሰብዓዊ መብቶች ረግጧል፤ የቤተ ክርስቲያኗን ሥርዓት በመጣስ ፓትርያርኩን ሽሮ የራሱን ካድሬ ሹሟል። አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ የዋልድባ ገዳም እና የቅዱሳን መካነ መቃብርን ደፍሯል። ይህንን ሃቅ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ ሙስሊሞችም ያውቃሉ። ለዚህም ነው "እኛ አንከፋፈልም!" እያሉ ያለው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አንዴ ከክርስቲያኑ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሙስሊሙ ጋር የወገነ እየመሰለ ኢትዮጵያዊውን ሙስሊምና ክርስቲያን ለማጣላት ለዓመታት ሲጥር መቆየቱ በይፋ የሚታወቅ ነገር ነው። ወያኔ በተለያዩ ቦታዎች በካድሬዎቹ አማካይነት በሃይማኖት ሰበብ ግጭቶችን ሲቆሰቁስ መኖሩ የአደባባይ ምስጢር ነው። በመጠኑም ቢሆን ይህ ተሳክቶለት ነበር። አሁን ግን ህዝብ ይህን ተንኮል በሚገባ ስለተረዳ ከዚህ በኋላ የሚሰራለት አይሆንም።

ሰሞኑን ከክርስቲያኑም ከእስልምናም የሃይማኖት አባቶች ተመሳሳይ የትግል ጥሪዎች እየደረሱ ነው። በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና በምዕመናኑ ላይ የሚያደርሰው የመብት ረገጣ እየከረረ በመምጣቱ ምዕመናን ጠንከር ያለ ምላሽ እንዲሰጡ የሃይማኖት አባቶች ጥሪ አድርገዋል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በእስልምና ሃይማኖታዊ አስተምህሮት ጉዳይ ጣልቃ በመግባትም ሙስሊሙን ማኅበረሰብ እርስበርስ ለማጋጨት ያደረገው ሙከራ ከፍተኛ ቁጣ አስከትሏል። የሙስሊም የሃይማኖት አባቶች የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለመብቶቻቸው እንዲቆሙ ጥሪ አድርገዋል።

"ታሪክ ራስዋን ትደግማለች" እንዲሉ በ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት ሙስሊም ማኅበረሰብ የተጫወተው አቢይ ሚና የሚያስታውስ ተግባር መታየት ጀምሯል።

በ1966 ዓም አዲስ አባባን ያጥለቀለቃት የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ሰልፈኛ ያዜመውን

ክርስትያኖች ወገኖቻችን
ተሰለፉ ከጎናችን
እንድንሠራ ለሃገራችን!!!
ሃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው፣
የሚለው መሪ ቃል ቢከበርስ ምን ነው?

እንደገና መዜም ተጀምሯል።

በአለፈው አርብ አወሊያ መስጊድ የተገኙ ሙስሊሞች በስግደት በኋላ የተለመደው የተቃውሞ ድምጽ ሲያሰሙ በርካታ ክርስቲያኖች ድጋፋቸውን አሳይተዋል። በካናዳ ደግሞ በዋልደባ ገዳም ላይ ወያኔ እያደረሰው ያለውን ጥቃት ለመቃወም ከወጡ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊያን ጎን ሙስሊሞችም ታይተዋል። የሁለቱ ሃይማኖቶች ምዕመናን ሲጋራ መብቶቻቸውና በጋራ የሚቆሙበት ደረጃ ላይ መድረሳችን አሁን ያለንበትን አዋራጅ የባርነት ጊዜ የሚያሳጥርልን ሠናይ ነገር ነው። መለስ ዜናዊ እና እኩይ ቡድኑ በሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ በአገራችን ውስጥ የሙስሊሙም ሆነ የክርስትያኑ መብቶች እንደማይከበሩ ለሁሉም ወገኖች ግልጽ እየሆነ መጥቷል።

አሁን የቀረን አንድ ወሳኝ እርምጃ ነው።

መለስ ዜናዊ ከሥልጣን እስካልተወገደ ድረስ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች አንዳችም መብት፤ አንዳችም ነፃነት እንደማይኖራቸው ማመን ይገባል። ይህ እምነት ደግሞ እያደር በሁሉም ወገኖች ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ ነው።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እየታየ ያለው መልካም ጅማሮ ስር እንዲሰድና ፍሬ እንዲያፈራ ጠንክሮ ይሠራል። ግንቦት 7፣ ሙስሊምም ሆነ ክርስቲያን የሆንን ኢትዮጵያዊያን በሙሉ "መለስ ዜናዊ ቁርጥህን እወቅ፤ እኛ አንለያይም!!!" እንድንለው ይጠይቃል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!. . .** (ከገፅ 1 የዞረ)

## በስዊዘርላንድ እና ኣካባቢዋ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ጄኔቭ በሚገኘው በተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት ፊት ለፊት ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ኣካሄዱ

የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው ባጠናከረው ዜና ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን በትናንትናው ዕለት ረቡዕ ሚያዚያ 17 ቀን 2004 ዓም ጀኔቭ ከተማ በሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት ፊት ለፊት በመሰባሰብ የወያኔ አገዛዝ በህዝባችንና በአገራችን ላይ እየፈጸመ ያለውን ወንጀል አለም አቀፍ ህብረተሰብ ይረዳልን ሲሉ በሰላማዊ ሰልፍ ጠይቀዋል።

ሰላማዊ ሰልፉን ያዘጋጁት በስዊዘርላንድ ነዋሪ የሆኑ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅት ደጋፊዎች፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ኣባላት፣ የተዋህዶ ኦርቶዶክስና የእስልምና እምነት ተወካዮች እንዲሁም ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን እንደሆኑ የገለጸው ዘጋቢያችን፤ ሰላማዊ ሰልፉ የተደረገበትን አንኳር ምክንያቶችን በዝርዝር የሚያስረዳ የአቤቱታ ደብዳቤ በጋራ አዘጋጅተው ለተባበሩት መንግስታት የሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር ፣ ለተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና ባህል ድርጅት፣ ለኣለም ኣብያተ ክርስቲያን ጽ /ቤት ፣ ለኣለማቀፉ የቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማህበር እንዲሁም ለተለያዩ ኣለም ኣቀፍ ተቋማት ማስገባታቸውን አስታውቀዋል።

ሰላማዊ ሰልፈኞቹ ወያኔ "ዋልድባ ገዳምን ለማፍረስ እየወሰደ ያለውን እርምጃና በሁሉም የእምነት ተቋማት ላይ እያካሄደ ያለውን ጣልቃ ገብነት በጽኑ በመኮነን ድርጊቱን በአስቸኳይ እንዲያቆም ከመጠየቃቸውም በላይ፣

- የሽብርተኝነት ታርጋ እየለጠፈ በንጹሐን ዜጎች ላይ የሚያካሄደውን አፈናና የመብት ረገጣ ፣
- የዜጎችን ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት በመገደብ በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለውን መፈናቀል ፣
- በኢንቨስትመንት ስም በውጭ ባለሀብቶች አማካይነት እየተካሄደ ያለውን የመሬት ቅርምትና የዜጎች ከቀያቸው መፈናቀል ፤
- መምህራን ያቀረቡትን የመብት ጥያቄ በአግባቡ ከመመለስ ይልቅ ጥያቄውን ለማዳፈን እየተከሄደበት ያለውን መንገድ በመቃወም
- በአጠቃላይ ሐገራችን ኢትዮጵያ አሁን ለምትገኝበት አስከፊና አሳዛኝ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ ድህነት፣ በሽታና ድንቁርና የዳረጋት የወያኔ ብልሹ አሰራር በመሆኑ ጨቛኝና አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአስቸኳይ ስልጣኑን እንዲለቅ ጠይቀዋል።

ሰለፈኞቹ ሲያሰሟቸው ከነበሩት መፈክሮች መካከል፤ ወያኔ ሌባ ነው፣ መለስ ዜናዊ ሽብርተኛ ነው : መለስ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ዘረኝነትና ከፋፋይነት ይብቃ፤ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች አሁኑኑ ይፈቱ፤ በዜጎቻችን ላይ የሚፈጸመው አፈናና ጭቆና ይቁም፤ የእምነት ነጻነት ይከበር፤ ሁሉም ሃይማኖት እኩል ነው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህ የለም፤ ጭቆናና ዘረኝነት ይቁም ፤ ዲሞክራሲ በአገራችን ይስፈን ወዘተ የሚሉ ነበሩ፤።

ወያኔ የእምነት ተቋማትን ለማፍረስና ምዕመናኑን ለመከፋፈል እያደረገ ያለው አዲሱ ዘመቻ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጭምር አጅግ አስቆጥቶአል።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ያቀረበውን የመብት ጥያቄ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መኖሩ ተደርሶበታል" ማለቱ ብዙዎችን እንዳስቆጣና ባለፈው አርብ ቁጥሩ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ በተቃውሞ በነቂስ እንዲወጣ እንዳደረገው ታውቆአል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት የተባለው በህዝበ ሙስሊም ተቃውሞ የገጠመው ተቋም እንደርሱ በተለያዩ ክልል ከህዝብ የተነጠሉ ኡላማዎችን ሰብስቦ፣ ከዞን እና ከወረዳ ምክር ቤት ሀላፊዎች ጋር በጋራ ተመካክሮ ባሳለፈው አቋም፣ የአክራሪነት መንፈስ የተጠናወታቸው አካላት ህዝበ ሙስሊሙ ሀይማኖቱን ተረጋግቶ እንዳያካሂድ እያደረጉት በመሆኑ፣ ህብረተሰቡና የጸጥታ አስከባሪዎች ግለሰቦቹን እየያዙ ለህግ ማቅረብ እንዳለባቸው ሰሞኑን ውሳኔ ማስተላለፉ፥ መለስ ዜናዊ ሊወስደው ላሰበው የሃይል እርምጃ መሰናዶ እንደሆነ ይነገራል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሆነው የወያኔን ጣልቃገብነት በሃይማኖቱ ውስጥ እያስተናገዱ ያሉት (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ሃይለ ሀሳብ
የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 206 ሚያዝያ 18 2004 ገጽ

# በአገራችን ላይ የተከፈተውን የጠላት ዘመቻ ለማስቆም መፍትሄው መተባበር ብቻ ነው !!!

ትልቅ ጆሮ ያላቸው ግን ደግሞ በጥሞና ማዳመጥ የማይሆንላቸው፤ ትልቅ ዓይንም እያላቸው አርቀው ማየት የተሳናቸው እንስሶች አህዮች ናቸው። እነዚህ አህዮች ግን ማንነታቸውን የሚያጠፋ፤ ሥጋቸውን ለመቀራመት የመጣን ጅብ ለመከላከል ፊታቸውን ወደፊት አዙረው በኋላ እግራቸው ያን ጅብ በእርግጫ አጡዘው ከጥፋት የመዳን ልማድ አላቸው። ተፈጥሮ ከሚያስተምረን ብዙ ቁም ነገሮች መካከል አንዱ ይሄው ነው።

ዛሬ በአገራችን ታሪካችንን የሚጣፋ፤ ማንነታችንን የሚያዋርድ ኢትዮጵያዊያንንንም የማያውቅ፤ ሰማይንና ምድርን የሰራን እግዚአብሄርን የማይፈራ የውስጥ ጠላት ተነስቷል። ይህ ደመኛ ጠላት አገራችንን በታሪኳ አይታ የማታውቀው ቀውስ ውስጥ እየከተታት ነው። ይህ የውስጥ ጠላት ታሪካችንን ለማዋረድ ብርቱ ጥረት አድርጓል፤ ማንነታችንንም ሊያጠፋ ያልፈጸመው እኩይ ተግባር የለም። ምንም እንኳ አገራችን ብዙዎች የመሰከሩላት የረዥም ግዜ ታሪክ ባለቤት ብትሆንም ቀንደኛው ጠላታችን መለስ ዜናዊ “ኢትዮጵያ የምትባል አገር ታሪክ የላትም፤ ካላትም የአንድ ሽማግሌ እድሜ ታሪክ ነው ያላት” ማለቱን የምንረሳው አይደለም። በአገራችን ታሪክና በማንነታችን ላይ ጣቱን የቀሰረው ይህ ዘራፊና ዘረኛ ቡድን ቀጣዩን ጥቃት ደግሞ በእምነት ተቋማት ላይ አድርጓል።

በመጀመሪያ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን አፍርሶ የራሱን ካድሬ በቤተ-ክርስትያን ራስ ላይ በመሾም የምእመናኑ አንድነት አፈረሰ ከዚያም ቤተክርስትያን የሌቦችና የቀማኞች ዋሻ በመሆኗ የአንዲት ቤተክርስትያን ልጆች ከሁለት ጎራ በላይ ተከፈሉ።

ይሄን ተከትሎ በርካታ የታሪኮቻችንን ትላልቅ ቅርሶችና መዛግብትን የያዙ ለዓይኖቻችን ማረፊያ፤ ለጆሮአችንም ብዙ ድንቅ ነገር የምንሰማባቸው በዓለም ታውቀውና ክበር ተሰጥቷቸው የቆዩ አድባራትን ማፍረስ ጀምሯል። የምእመናኑንም አጽም አውጥቶ ሜዳ ላይ በመጣል መሬቱን ለሸንኮራ አገደ ልማት በማለት ለባእዳን አሳልፎ እየሸጠ ነው። ይሄ የጠላት ተግባር እንጂ ለአገሩ ክብር የሚቆረቆር ቡድን ተግባር አይደለም። አብዛኛው የአገራችን ታሪክ የተቆራኘው ዛሬ መለስ ዜናዊ እየነጠቀ ለሸንኮራ አገዳ ልማት በሚል ሰበብ እየቸበቸበ በሚገኘው የአድባራቱ መሬት ላይ ነው። ለመለስ ዜናዊና ጀሌዎቹ የታሪካችን አምዶች ከሸንኮራ አገዳ አይበልጡምና የአገሪቷ የታሪክ ቅርሶች የቆሙበትን መሬት በሙሉ ማጥፋት መለስና ጉጅሌዎቹ የቆሙለት ቋሚ ተልእኮ ነው።

ምንም ዓይነት እምነት ብንከተል ዛሬ መለስና ጉጅሌዎቹ ሊያወድሙት የተነሱት ገዳማት የማንነታችን መገለጫዎች በመሆናቸው ሃብቶቻችን መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

መስጊዶቻችንም እንደ አድባራቱ ሁሉ ብዙ ድንቃ ድንቅ ታሪኮቻችንን የያዙ ናቸው። ዛሬ መለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ተሰምቶ የማይታወቅ ዘመቻ ጀምረዋል። አንዱን ጥሩ ሙስሊም ሲሉ፤ ሌላኛውን ደግሞ ከጽንፈኛ አሸባሪዎች ጋር እያስተሳሰሩ በዜጎች ላይ የሚያድረሱት ግፍ ከግዜ ወደ ግዜ ከምን ግዜውም በላይ ተጠናክሮ ቀጥሏል። የእምነት ነጻነታችን ይከበር ያሉ ሙስሊሞችን ጽንፈኛ አሸባሪዎች ናቸው ማለት መለስ ዜናዊና ጀሌዎቹ የደረሱበትን የአሸባሪነት ደረጃ የሚያመለክት ነው። መለስ ዜናዊ ሙስሊሙን ማህበረሰብ ለሁለት ከፍሎ ሁከት የሚፈጥረው በአጣቃላይ በኢትዮጵያዊያ ላይ ካለው ጥላቻ የመነጨ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።ሙስሊሙ ማህበርሰብ ጎሳ ለይቶ ርስ በርሱ የማይጋጭ፤ በጎሳ ከመከፋፈል ይልቅ አንድ መሆን ይሻለናል የሚል ጠንካራ እምነት ያለው ማህበረሰብ ነው።መለስ ዜናዊ የሚጠላው እና ሊያተራምሰው የተነሳውም ይሄን የረጋ አንድነት ነው።

ህዝቦች አንድ የሚሆኑበት ነገር ለዘረኞችና ለዘራፊዎች ቅዥታቸው ነው።ይሄ ቅዥታቸው በሚችሉት ሁሉ አንድነቱን አናግተው ያን ህዝብ አዋርደውና ረግጠው ለመግዛት ብዙ እኩይ መንግዶችን እንድሄዱ አድርጓቸዋል። እነመለስ ዜናዊ የሚሄዱባቸው የጥፋት መንገዶች አገራችንን የከፋ ሁከት ውስጥ የሚከቱ መሆናቸውን ይህን ዘረኛና ዘራፊ ቡድን እየተከተሉ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ሊገነዘቡት ይገባል።

ዛሬ አገራችን ባለችበት ሁኔታ ከልዩነቶቻችን ይልቅ ማንነታችንን ሊያጠፉ፤ ደማችንንም በከንቱ በየሜዳው ሊያፈስ የተነሳው ጠላት እጅግ የከፋ ነው።መብታችንን በጠይቅን ግዜ አሸባሪ ብሎ የመከራ እንጀራን ሊያበላን፤ የመከራ ጽዋንም ሊያጠጣን የተነሳ ኃይልን ለሃያ ዓመታት በጫንቃችን ላይ ተሸክመነው ኑረናል። ይሄ ዘረኛና ዘራፊ ቡድን በቃህ የሚባልበት እውነተኛው ግዜ አሁን ነው። በክርስትያኑ እንባ ሙስሊሙ አይስቅም፤ በሙስሊሙ እንግልትም ክርስትያኑ ደስ አይሰኝም። ክርስትያንና ሙስሊሙ አንድ ላይ በመቆም ፍትህ የነገሰባት፤ ነጻነት የሰፈነባት፤ የህግ የበላይነት የተከበረባት፤ ዜጎች በሙሉ ከጎሳ ቆጠራ ወጥተው በገዛ አገራቸው በህግ ማእቀፍ ሥር የፈለጉትን እምነት ተከትለው የሚኖሩባትን አገር ለመፍጠር በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ይህን ህያው ጠላት በቃህ ለማለት መሰባሰብ፤ ከልዩነት ይልቅ የጋራ ጠላት ላይ ማተኮር፤ ራስን ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ለመከላከል አብሮ መቆም ግዜው የሚጠይቀው ታሪካዊ ግዴታ ነው። ምንም ከማይገኝባት ከዚያች አህያም መማር ያለብን እውነት በጋራ ሆኖ አንድ ላይ ገጥሞ ጠላትን መመከትን ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን !!!**

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ያሰፈነውን ኢፍትሃዊነት በመቃወም አዲስ አበባ ከተማ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ይጮህ እንደነበረ የገለጹት ምንጮች በሰዎች ርብርብ እሳቱን ማጥፋት እንደተቻለ ሆኖም ግን ከአይኑ በቀር በመላው አካላቱ ላይ ከፍተኛ የቃጠሎ አደጋ እንደደረሰበት እና በፖሊስ ፓትሮል መኪና ለህክምና እርዳታ ወዲያውኑ ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል እንደተወሰደ ገልጸዋል።

አደጋው እንደደረሰ በፍጥነት ሥፍራው የደረሰው የፌዴራል ፖሊስ በሁኔታው አዝነውና ተቆጥተው ሲጯጯሁ የነበሩትን ሰዎች አግቶ በአቅራቢያው ወደሚገኝ አንድ ቅጥር ጊቢ ወስዶአቸው እንደነበርና የሞባይል ስልካቸውን በመንጠቅና በማስፈራራት ከሰአታት በኋላ እንደለቀቃቸው የዘገበው የግንቦት 7 ዘጋቢ ዜናው እንዳይዘመት ስጋት የገባው ፈደራል ፖሊሲ በስፍራው ተገኝቶ የቀረጻ ሥራ ይሰራ የነበረውን የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ሪፖርተርና የካሜራ ጋዜጠኛ ቡድን ለማስቆም ጥረት አድርጎ እንደነበረ ሆኖም ማንነታቸውን ካረጋገጠ ቦኋላ እንደተዋቸው ዘግቦአል።

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ትናንት ባቀረበው ዘገባ በ6 ኪሎ የሚማሩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እራሱን ያቃጠለው ወጣት ጉዳይ እንዲጣራ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ሞክረው በፖሊስ እንደተበተነ ታውቆአል።

በኢሳት ዘገባ መሰረት የተወሰኑ የዩኒቨርስቲው ተማሪዎችም ተጎጂው ወጣት ለህክምና ተኝቶበታል በተባለው የካቲት 12 ሆስፒታል ተሰብስበው ለመግባት ያደረጉት ሙከራም በፖሊስ ተበትኗል።

በአገሪቱ ውስጥ በሰፈነው አፈናና ማህበራዊ ቀውሶች ተስፋ ቆርጦ እራሱን ለማጥፋት ሙከራ ያደረገው ወጣት የአዲስ አበባ ፖሊስ በ1998 ዓ.ም በፖሊስነት ከቀጠራቸው ምልምሎች አንዱ የነበረ ሲሆን በሰራዊቱ ውስጥ ያለውን አድሎአዊነትና ኢፍትሃዊነት ለመቀበል ባለመቻሉ በአሻጥር ከሥራው እንዲገለል የተደረገ መሆኑን ስማቸዉን ለመግለጽ ያልፈለጉ ነገር ግን ለግለሰቡ ቅርበት አለን የሚሉ ሰዎች ለኢሳት ዘጋቢ ገልጸዋል ተብሎአል።

የአዲስ አበባ መርማሪ ፖሊሶች በትናትናው ዕለት የጉዳቱ ሰለባ የሆነው ግለሰብ ለህክምና እርዳታ በተኛበት የየካቲት 12 ሆስፒታል ውስጥ ለምርመራ ቃሉን እንደተቀበሉት ለኢሳት የገለጹ የሆስፒታሉ ምንጮች የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ድርጅት /ኢቲቪ/ ሆስፒታል ክፍሉ ውስጥ ገብቶ ቀረጻ እንዳካሄደና የሆስፒታሉ የህክምና ባለሙያዎችና ነርሶች ለመቀረጽ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ተገቢ ህክምና እየተደርገለት መሆኑን ለማሳየት እንዲቻል ብቻ የህክምና እርዳታ በማድረግ ላይ እንዳሉ እጃቸው ካሜራ ቀረጻው ውስጥ እንደገባ ገልጸዋል።

እንደ ኢሳት ምንጮች በራሱ ላይ እርምጃ የወሰደው ግለሰብ የፖሊስ አባል እንደነበር ከታወቀ በኋላ የፌዴራል ፖሊስና የደህንነት ሠራተኞች ጓደኞቹን የማዋከብና ምንም እንዳይተነፍሱ ለማድረግ እየሞከሩ ነው።

ከ4 ወራት በፊት መምህር የኔሰው ገብሬ የተባለ የዋካ ነዋሪ ፍትህ በሌለበት ከመኖር መሞትን እመርጣለሁ እያለ የወረዳውና የዞኑ ባለሥልጣናት በተሰበሰቡበት ቢሮ ፊት ለፊት ራሱን በእሳት አቃጥሎ ከገደለ በሁዋላ፣ በተለያየ ቦታዎች ዜጎች ህይወታቸውን በምሬት ማጥፋታቸው መዘገቡ ይታወሳል። በደብረማርቆስ ከተማ አንድ የትግራይ ተወላጅ በቅርቡ ራሱን ማቃጠሉን ፍኖተ ነጻነት ዘግቦአል። በደቡብ ክልል በርካታ አርሶ አደሮች ራሳቸውን ገደል ውስጥ እየወረወሩ አጥፍተዋል።

ዘርን መሰረት ባደረገ የወያኔ አድሎአዊ ፖሊሲ ተማረውና በአገራቸው ተስፋ አጥተው ወደ ጎረቤት አገሮችና የአረቡ አለም በየብስና በባህር ከሚሰደዱ በሺዎች ከሚቆጠሩ ዜጎች በተጨማሪ በረሃብና በስራ አጥነት ምክንያት ህይወታቸውን ለማቆየት ሲሉ በዘረፋና በተለያየ ወንጀሎች የተሰማሩ ሰዎች ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ ይታወቃል።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ያቀረበውን የመብት ጥያቄ . . . (ከገፅ 2 የዞረ)

ሼህ አህመዲን ሼህ አብዱላሂ ባለድርሻዎች አክራሪዎችን እየመረጡ ወደ ህግ እንዲያቀርቡዋቸው መጠየቃቸው በርካታ የሙስሊም እምነት ተከታዮችን እያስቆጣ ነው።

በመላው አገሪቱ የሚገኙ የሙስሊም እምነት ተከታዩች በአወሊያ የተነሳውን ህዝባዊ ጥያቄ በመደገፍ ድጋፋቸውን እየገለጹ እንደሆነ የገለጸው ዘጋቢያችን ባለፈው አርብ በደሴ፤ በጂማና በሃረር በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወጥተው ድጋፋቸውን መግለጻቸውን አስታውሶአል።

የሙስሊሙ ህብረተሰብ ያነሳው የመብት ጥያቄ ግልጽ ሆኖ ሳለ የክርስትና እምነት ተከታዮች ጥርጣሬና ፍርሃት እንዲያድርባቸው አገሪቱ በእስላማዊ የሼሪያን ህግ እንድትተዳደር ይፈልጋሉ የሚል የፈጠራ ወሬ በመለስ ዜናዊና በካድሬዎቹ እየተሰራጨ እንደሚገኝ ይታወቃል። ባለፈው የጁማ ጸሎት ወቅት ፕሮግራሙን የመሩት አባቶች ክርስቲያን ወገናቸው ከጎችናቸው እንዲቆም ጥሪ ማስተላለፋቸው ይታወሳል። በ1966 ዓም ሙስሊም ህብረተሰብ አንስቶት የነበረውን የመብት ጥያቄ ህዝበ ክርስቲያኑ በነቂስ ወጥቶ ደግፎት እንደነበረ ይታወሳል።

## የዘረኛው ወያኔ መሪዎች እስካሁንም የአልባንያ ኮሚኒዝም ተከታይና አቀንቃኝ መሆናቸውን በተግባር እየገለጹ ነው ተባለ

የአንድነት ልሳን የሆነው ፍኖተ ነጻነት እንደገለጸው የአልባኒያን ኪሚኒዚም ተከታዮች የነበሩት የህወሃት መሪዎች ዲሞክራቶች ይሆናሉ በሚል ግምት የምዕራቡ ዓለም ላለፉት 20 አመታት የቸራቸውን ሁለ ገብ ድጋፍ ከመጠፍ ባለመቁጠር በኮሚኒስቲነታቸው የቀጥሉ መሆናቸውን በተግባር እያረጋገጡ ናቸው በማለት "ህወሃቶች ቀድሞውኑም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ሀሳብን ለመግለጽ ነጻነት አልታገሉም። የታገሉት ለአንድ ነገር ብቻ ነው -ያም ለስልጣን ነው" ብሎአል።

ከ1997 ዓ/.ም ምርጫ በኋላ ዘረኛው ወያኔ ማርሽ ቀይሯል። ማርሽ ቅየራውም ከጭላንጭል ዴሞክራሲ ወደ ለየለት አምባገነን ሥርዓት፣ከመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ወደ አንድ ፓርቲና ነጻ ሚዲያን ማየት ወደማይሻ ሥርዓት ነው። እንዲህ ዓይነቱ አክሮባት ዋና ግቡ ደግሞ በግድም በውድም ጠቅልሎ መግዛት ነው - እንደ ፓርቲው ልሳን።

ከጅምሩ የትግራይን ሪፐብሊክ ለመመስረት የታገለው ዘረኛውና ጠባቡ ወያኔ በለስ ቀንቶት መላ ሀገሪቱን መቆጣጠር ችሏል። ታዲያ ያኔ የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ ነበርና የፕላኔታችን ብቸኛ ልዕለ ሃያል ሆና የወጣችው ዩናይትድ ስቴትስ ዶላርና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታን በመቀላቀል ወያኔን ጋተችው ። ዘረኛው ወያኔም አማራጭ ስላልነበረው የአልባንያ ኮሚኒዝም ማሊያውን አውልቆ ዲሞክራት የሚል ማሊያ ለበሰ። የማሊያ ለውጥ የአመለካከት ለውጥ አይደለምና ይሄው ዛሬም ከ20 ዓመት በኋላ፣ ድመት መንኩሳ ... እንዲሉ ወያኔም ይዞት ወደ ተነሳው የዘር ጥላቻ፣ጸረ ዴሞክራሲያዊነትና አምባገነንነት በግልጽ ተመልሷል።

ይሄውም ይላል ፍኖተ ነጻነት፤ በዛ በዝረራ ከተሸነፈበት ምርጫ በኋላ የቀየረውን የዴሞክራት ማሊያ አውልቆ ወደነበረበት የተመለሰው ዘረኛው የወያኔ ስርዓት አሁን ሀቀኛ ተቃዋሚዎችንና በጽናት እየሰሩ ያሉ አንድ አንድ ነጻ ጋዜጦችን በጠላትነት ፈርጀ ሊያጠፋቸው የሚችለውን ሁሉ እያደረገ ነው።

በመሆኑም የማይገናኝ ህግ እያጣቀሱ መፈረጅ፣ ነጻ ጋዜጦችን ለማጥፋት መትጋትና ሀቀኛ ተቃዋሚዎች ላይ ስም በመለጠፍ ከህዝብ ለመነጠል የሚሰሩ ደባዎች በሀገር ላይ የሚደረጉ ደባዎች በመሆናቸው በጽኑ እቃወማቸዋለሁ ብሏል አንድነት።

ፖለቲከኞችንና ጋዜጠኞችን እንዲሰደዱ በማድረግ ወይም እስር ቤት በማጎር የህዝብን የነጻነት ስሜት ማፈን አይቻልም፤ ትውልድ ካልቆመ በስተቀር ይህ ስሜት ሊዳፈንም ሊቆምም ከቶውንም አይችልም ያለው ፍኖተ ነጻነት ሚስማር አናቱን በመቱት ቁጥር ይጠብቃል በማለት ለዘረኛው የወያኔ ስርዓት እውነታውን ፍንትው አድርጎ አሳይቷል።

ዘረኛው ወያኔ ያለውን የከፋት ስልት አንጠፍጥፎ የሚጠቀምበትንና የኢትዮጵያ ህዝብ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ የሚያውቀውን ያረጀ ያፈጀ ስልት ደግሞ ፍኖተ ነጻነት እንዲህ ገልጾታል ፣ወያኔ አንድ ጋዜጣ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ሲገነዘብ በመጀመሪያ በመጽሄቱ አዲስ ራዕይ፣ቀጥሎም በአዲስ ዘመንና በአይጋ ፎረም፣ ከዛም በራዲዮና በቴሌቪዥን የካድሬዎች የውይይት አጀንዳ ያደርገዋል፣አከታትሎም በሽብር ተግባር ሲንቀሳቀሱ ተገኙ በሚል ተራ ጨዋታ ዜና ይሰራበታል፤በመጨረሻም ጋዜጠኞቹ እንዲሰደዱ ወይም እስር ቤት እንዲወረወሩ ይደረጋል።እናም የዚህ የወረደ ስልት የአሁኗ ተረኛ ዒላማ ፍትህ ጋዜጣ ነች ብሏል።

ከመሬት እየተነሱ ሽብርተኛ በማለት ጣት መጠቆም መዘዙ ለራስ ይተርፍል።የህዝብ ብሶት መፈንጃው አይታወቅም፤ያኔ ለሌሎች በቆፈሩት ጉድጓድ መግባት ይኖራል።በመሆኑም ከወዲሁ ቆም ብሎ እውነታውን ማጤንና ለዚች ምስኪን ሀገር ማሰብ ይበጃል ሲል አንድነት በልሳኑ በፍኖተ ነጻነት አሳስቧል።

## ምኞትና ስኬት

ወንዶችም ሴቶችም ስለወደፊቱ
የትዳር ጋደኛ መልክና ቁመቱ
ፀባይና ቀለም የቁንጅና አይነቱ
የተለያየ ቢሆንም የሰው ልጅ ምኞቱ
መሻትን ነው እንጂ መች ታውቆ ስኬቱ
የሰው ልብ ይመኛል እግዜር ይፈጽማል
የጠሉት ይወርሳል የፈሩት ይነግሳል
የታሰበው ቀርቶ ያልታሰበው ይሆናል
አብሮ መኖር እንጂ ቀባሪን ማን ያውቃል
ተሳካ አልተሳካ ሁሉም ሰው ይመኛል
ቀጭን ዘለግ ያለች ሸንጣም ሲመኝ ኖሮ
አራት ወልዶ ስሞ ከወፍራም ስንዝሮ
አመስግኖ ይኖራል ሰጪውን አክብሮ
ሴትና ሽምብራ ሲያጥር ነው እያለ
ስንቱ በቆጥ ፍቅር ማማ ተሰቀለ
አይነ ዛጎል ሲመኝ አይኖቿ ከብላላ
ቻይናዊ አግብቶ ይኖራል በተድላ
ጥርሰ-በረዶዋን ሲመኝ ቀጭኗን
ወርቃማጥርሶቿን ሳያየው ቦርጯን
ሲያደንቀው ይኖራል ድብቅ ውበቷን
የቄስ ልጅ ክርስቲያን ሲመኝ የነበረው
ስንቱ ነው ለፍቅር በፍቅር የሰለመው
የተማረች ሲመኝ ቀለም የገባት
ከቤት ሰራተኛው ፊደል ካላያት
ተጋብቶ ተዋልዶ አለፉ ዓመታት
ዋናው መከባበር ከልብ መግገባባት
የሃብታም ልጅ አግብቶ መኖር የሚመኘው
ደሃዋን ይጠልፋል እግዜር ይሁን ሲለው
ቁመናው ዘንካታ ደረቱ የሰፋ
ስትመኝ ቆይታ በጉልበት ተጠልፋ
ከአጭሩ ቀጭኑ ጎጆዋን ቀልሳ
የእህል ውሃ ነገር ጥልፊያውም ተረሳ
የተመኙት ቀርቶ ያላሰቡት ሆኖ
በፈለገው ሳይሆን በተሰጠው አምኖ
ተሳካ አልተሳካ ህይወት ይቀጥላል
ታዲያ አብሮ አደጎች ሲገናኙ ኖረው
ዛሬን ሲመዝኑ ከድሮ አወዳድረው
ምኞትና ስኬት ወሬ እንደሆኑ አውቀው
ዉበትን በፀባይ በፍቅር ሸፍነው
አይንና ቅንድብን በልብ ተክተው
አፍንጫን ደረትን በእስተንፋስ ለውጠው
ምኞት ቅጀት እንጂ ተስፋ እንዳልሆነአውቀው
በደስታ ይኖራሉ ትዳርን መስርተው
ጎጆ ለመመስረት በትዳር ለመርካት
ልጅ ወልዶ ለመሳም ዘርን ለመተካት
መቼ ይበቃና ቁንጅና ደም ግባት?
መጨቃጨቅ ቢኖር መፋቀር ካልጠፋ
ተቻችሎ ይኖራል ተሳስሮ በተሰፋ
መደማመጥ ጠፍቶ ሲያንዣብብ አደጋ
ሰማንያ ተቀድዶ ይለያያል አልጋ
እኔ ለሃገሬ የምመኝላት እንዲሳካላት
ለኛ በኛ የቆመ የጦር ሰራዊት
በምርጫ የመጣ ህዝባዊ ስርአት
ሰው በሰውነቱ ሚከበርበት
የህግ የበላይነት የሚታይበት
መሬት ሲለማ እንደግል ሃብት
እኔ ለሃበሻ ህዝብ የምመኝለት
ማትሪክ ከአስራ ሁለት--የነጻ ቲቪ ጋዜጣ መጽሄት
በነጻ የመናገር የመሰብሰብ መብት
የነጻ ፍርድ ቤት ግልጽ ዳኝነት
ብዙ ትምህርት ቤት ትንሽ እስር ቤት
እኛ የተመኘነው የፈለግነው መሪ
ለሃገር ተቆርቋሪ ህግና ደንብ ፈሪ
እውነት ተናጋሪ አምነትን አክባሪ
የተማረ አክባሪ አንድነት ፈጣሪ
እኛ ያልተመኘነው ይጥፋልን ምንለው
የውሸት ፓርላማ ተኝቶ ሚውለው
የሚሰድበን መሪ ራበን ስንለው
ገዳምና መስጊድ የሚያፈራርሰው
ያለጥፋት ይዞ ያለፍርድ የሚያስረው
ጎተራ አፍርሶ ከርቸሌ ሚያደርገው
ተቃዋሚን ሁሉ አሸባሪ የሚለው
መበታተን እንጂ መሰብሰብ ሚቀፈው
ጅምላና ችርቻሮ ቻረታ የሚወስደው
ምኞት ከንቱም ቢሆን ባለመሳካቱ
ከሌለ መቻቻል ፍቅሩ መግባባቱ
ባገር በባንዲራ በእምነት መስማማቱ
በፖሊስ አሿሿም በጦር ሰረዊቱ
በመሬት ሽያጩ ንግድ ድርጅቱ
ሰልፍ በመውጣቱ በመናገር መብቱ
በህገ መንግስቱ ተግባራዊነቱ
ምኞትና ስኬት እንዴት ይጣጣሙ?
አስር ሺ ጠይቀን ባንዱም ካልተስማሙ?
ሸራርፈው ለያይተው ሊያጠፉን ካደሙ?
ካቢኔውን ሞልቶት ባንዳና ኮንዶሙ
እጃችንን ብንሰጥ ለግንባር የሚያልሙ
ዛሬም እንደ ሽፍታ ዘርፈው የሚቀሙ
ጥንትም ሲፈጠሩ ለሃገር ያልቆሙ
ህዋሃትና ኢትዮጲያ እንዴት ይጣጣሙ?
ሃያ ዓመት አየነው እግዜርም አላለው
ከህዋሃት ጋብቻ ሳይተኙ ቅዠት ነው
ሳይሞቱ ኑዛዜ ማንኮራፋት ቆመው
ሽፍታ ባል አይሆንም በሌላ እንዳየነው
ሽፍጥም ስንቅ አይሆንም አብሮ ለሚጓዘው
ፊርማ እንዳንቀድድ ሰማንያ ውል የለው
ችሎት እነዳንሄድ መቼ ሰምቶን ደኛው
ሽማግሌ አይዳኘን ትዳሩ የጥልፊያ ነው
ሃብት እንዳንካፈል ለትግራይ ልማት ነው
ለማን አቤት እንበል ጦሩ የነሱ ነው?
ምኞት ባይሳካም ሃያ አመት ተለፍቶ
በጥልፊያ ተደፍሮ በግዳጅ ተጋብቶ
ኮንዶሙና ባንዳው አባ'ዱላው በዝቶ
እንዴት መላ ይጠፋል አባ መላ ሞልቶ?

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org